# ደብረ ዘይትና አባ ማትያስ

## "ዘያነብብ ለይለቡ (<u>አንባቢ ያስተውል</u>!)" (ማቴዎስ ፳፬፥፲፭)


**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@gmail.com


ሚያዝያ ፳፻፭ ዓ.ም.

***<u>ማሳሰቢያ</u>፦*** *በቀርቡ በወጣችው <u>ጦማር</u> ላይ "እንዲህ ያለ ፓትርያርክ አይተን አናውቅም" በሚል ርእስ እንገናኝ ብዬ በመሰናበቴ በዚህ ርእስ የሚቀርበውን አንባቢ እንደሚጠብቅ የታወቀ ነው። ይሁን እንጅ ያለፈው እሁድ ደብረ ዘይት የሚታሰብበት ቀን ስለነበረ፤ ይህች ጦማር የያዘችው መልእክት በከንሳስ ደብረ ሳህል መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቀረበ። ትምህርቱን የተካፈሉት ምእመናን በዓለም ዙሪያ ላለው ሁሉ ህዝብ ይድረስ" የሚል ሀሳብ ስላመነጩ "እንዲህ ያለ ፓትርያርክ አይተን አናውቅም" በሚል ርእስ የተዘጋጀውን ጦማር አዘግይቼ ይህችን ጦማር አስቀደምኩ። "እንዲህ ያለ ፓትርያርክ አይተን አናውቅም" በሚለው ርእስ የተዘጋጀው ጦማር ይቀጥላል።*

## <u>መግቢያ</u>

ደብረ ዘይት ተብላ የምትጠራው እሁድ ዘንድሮ መጋቢት ፳፱ ቀን ነበረች። በዚህች ቀን የሚነበበው ወንጌል ክርስቶስ በደብረ ዘይት ከሐዋርያት ጋራ የተናገራቸውን የያዘችው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፬ ናት። ይህች ምዕራፍ አካታ የያዘቻቸው <u>በዓለም መጨረሻ አካባቢ ስለሚከሰቱት ምልክቶች ነው</u>። የጥንት ኢትዮጵያውያን ይህች ምዕራፍ ከወንጌል ለይተው በብራና ጽፈው በትንሽ ቅርጽ አዘጋጅተው ማህደርና ማንገቻ አበጅተውላት በደረታቸው ተሸክመው በየደረሱበት ጥላ ስር ቁጭ ብለው ይደግሟት ነበር። ፍካሬ ኢየሱስ (**ልፋፈ ጽድቅ**) የሚል ስያሜ ሰጥተዋታል። ከዚህ ቀደም ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም. "ኢትዮጵያ በሶስቱ ፍካሬዎች" በሚል ርዕስ ባቀረብኳት ጦማር (http://medhanialemeotcks.org/pdf/FIKARE.pdf ) ፍካሬ ኢየሱስን መጥቀሴ ይታወሳል።

ፍካሬ ኢየሱስ (ልፋፈ ጽድቅ) የሚለው ቃል ከክርስቶስ አንደበት ለወጣው ለጠቅላላ ወንጌል ሊሰጥ የሚችል ቢሆንም፣ ኢትዮጵያውያን በተለየ መንገድ አዘጋጅተው ፍካሬ ኢየሱስ (ልፋፈ ጽድቅ) የሚለውን ልዩ ስም ሰጥተው ባንገታቸው አጥልቀው በደረታቸው ተሸክመው በየደረሱበት እንዲደግሟት እንዲያነቧት የሚያደረጉበት ምክንያት "ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተክቦ የምታዩት ይናዳል ይፈርሳል (ማቴ ፳፬፡ ፪ )" ብሎ ክርስቶስ በተናገረው አስደንጋጭ ንግግር ሐዋርያት ተገፍተው "የዓለም መጨረሻው ምልክት ምንድነው?" ብለው ለጠየቁት ጥያቄ ክርስቶስ የመለሳቸውን በመሸከሟ ነው።

ይህች ጦማር ኢየሱስ የሰጣቸውን ምልክቶች ሁሉ አካታ ለማቅረብ ከአቅሟ በላይ ስለሆኑ ያለንበትን ወቅት የሚያብራሩትን ምልክቶች ብቻ ከዚህ በታች ለማቅረብ እሞክራለሁ።

፩ኛ. የተቀደሰው ስፍራ

፪ኛ. በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ የሚታየው የጥፋት ርኩሰት

፫ኛ. አባ ማትያስ በፍካሬ ኢየሱስ

፬ኛ. ምን መደረግ አለበት?

ሀ. ወደ ተራራ ይሽሹ።

ለ. ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣ ከቤቱ ጣራ አይውረድ።

ሐ. "ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ" (፲፮-፲፰)

የተቀደሰው ስፍራ በሚለው በመጀመሪያው አንቀጽ እጀ ማራለሁ።

# ፩ኛ. <u>የተቀደሰው ስፍራ</u>

"<u>የተቀደሰው ስፍራ</u>" የቱ ነው? ይህ ስፍራ "ቅዱስ" እያልን አምላካችንን ከምንቀድስበት እና "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ" ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ማስጠንቀቂያ ከሚታወጅበት ከቤተ መቅደሳችን የተለየ ሌላ ስፍራ ሊሆን አይችልም። <u>ስለዚህ ስፍራ የተማርኩትንና የተጻፈውን ስናገር፣ እኔን እንደሚሰማኝ ርቆ ያለውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ በለበሰው ሥጋ በሚናገረው ቋንቋ በሚያነበው ፊደልና በሚበላው እንጀራ የኢትዮጵያዊነት ትዝታ የሚሰማው ይመስለኛል</u>። ይህ የጋራ የትዝታ ስሜት በተለያዩ ምክንያቶች ከነበረበት ቦታ ርቆ ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዜጋ እንዲዳስስልኝ፡ ዜግነታችንን የማይጋሩን ሊቅ የስፍራ ትዝታ የማይረሳ ረቂቅ ሰንሰለት እንደሆነ የገለጹትን ለዚህች አንቀጽ መንደርደሪያ ላደርገው ወደድኩ።

James Redfield የተባሉ ሊቅ, "The Celestine Prophecy and Adventure" በተባለው መ ጽሐፋቸው የዚህን አይነት የትዝታ ስፍራ "<u>channel of spiritual energy</u>" ወይም "<u>የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ</u>" ብለው ገልጸውታል። እኒህ ሊቅ "<u>የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ</u>"ብለው የገለጹት፣ ለኛ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችንን <u>ትመስላለች</u>። ሙሉ ሀሳባቸው እንደሚከተለው ነው። "we know that as the trascdent is achieved, began to feel more buoyant as though a channel of spiritual energy has began to inflate us from within"ማለትም የመንፈስ (ሞራል) እድገት ስሜት ብቅ ሲል የሚፈሰው መንፈስ ኃይል ውስጣችንን ያጥለቀልቀናል" ካሉ በኋላ እንዴት እንደሚከናወን እንዲህ ብለው ገለጹት። "This can occur during any of the mentioned

pathways to mystical, but …… All these objects now seem to have more presence and bearing even though they are far away. They litrally jump out at us and demand attention." ( 99)

***"አጋጣሚ ነገሮች በህይወታችን ድንገት ሲከሰቱ፤ ቀድሞ የሰማነው ያየነው በትዝታ መንፈስ "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ሆኖ በላያችን እንደ ደመና አንዣቦ ብቅ ይላል። በሩቁ ሰማይ እንደ ደመና ከሚያንዣብበው "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ንቃተ ህሊናችንን የሚቀሰቅስ የመንፈስ ደወል ድንገት ይሰማል።***

***በላያችን ደመና መስሎ የሚንሳፈፈው "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ጥንት የነበረውን ስሜት ቀስቅሶ ካዲሱ ክስተት ጋራ ያገናኝናል። እደ መንፈሳችንን ዘርግተን መንካት የምንችለው ቅርብ ይመስለናል። ተራሮች ዛፎች የበቀሉባቸው ቦታዎች፡ በየሸለቆው ያሉ ምንጮች ሁሉ "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ይከቡናል። ሩቅ መስለው ይታዩን የነበሩት እነዚህ ሁሉ አካላት ሰውነታችንን ባህር፤ ራሳቸውን ዋናተኛ አድርገው ከውስጣችን ዘለው ይገባሉ። ጥንት በውስጣችን የነበረውን ስሜት ቀስቅሰው ካዲሱ ክስተት ጋራ በማገናኘት የበለጠ ያድሱታል። ትኩረታችንን ሁሉ ይስቡታል ስሜታችንንም ይቆጣጠሩታል"ይላሉ።***

## በትዝታ የታደሰው የቤትወደድ ሱልጣን አሊ ሚራ ንግግር

***ታሪክን ታሪክ ይስበዋልና*** James Redfield ***የተናገሩትን ወደኛ ወደ ኢትዮጵያውያን ሳመጣው የተከበሩ ኢትዮጵያዊው አባት ቤት ወደድ ሱልጣን አሊ ሚራ ተናገሩ ተብሎ ሲነገር የሰማሁትን ጎተተው። ደርግ የጃንሆይን መንግስት ገልብጦ ኢትዮጵያ በተናወጸችበት ወቅት፤ ሳዳም ሁሴንና ጋዳፊ "አሁን ኢትዮጵያውያን የተዳከሙበት ኢትዮጵያን ወደ ተፈለገው አቅጣጫ ለመውሰድ አመች ጊዜ ነው። ኢትዮጵያውያን መንግስታቸውን ራሳቸው ደምስሰውታል። የቀረችውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ደምስሰህ ለመንገስ ላንተ ጥሩ አጋጣሚ ነው። መንገስ ትችል ዘንድ ወታደርና ጦር እንስጥህ" ቢሏቸው የተከበሩ ኢትዮጵያዊው አባት ቤትወደድ አሊ ሚራ "በኢትዮጵያተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ እናንት የምትሉኝን አላደርገውም። እኔና የአፋር ህዝብ ልናደርገው ቀርቶ የቤተ ክርስቲያኒቱን እጣን በማሽተት ግመሎቻችን ያውቋትልና ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የምትሉትን አላደርገውም" አሉ። በነ ሳዳም ሁሴን የተሰነዘረውን ጥፋት ለማቆም በተከበሩ ቤትወደድ ሱልጣን አሊ ሚራ ውስጥ የገባው በግመሉም ላይ ያንዣበበው*** James Redfield ***የተባሉት ሊቅ "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ብለው የገለጹት ነበር ከማለት ሌላ ምን ልንለው እንችላለን***?

***ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኔ ቢጤ ደካማ ካህናት ስህተት ካልተጋረደበት በቀር ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የብዙ ነገር ምንጩ የትዝታ እልባቱ "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ናት።የማህበር ጸሎት የሚከናወንባቸው ሕንጻወች በደረታቸው ሊሚሳቡ በእግራቸው ለሚሽከረከሩ በአየር ለሚበሩ ፍጥረታት ሁሉ መሰብሰቢያቸው ናት። በዚህ ፈታኝ ወቅት በቅጽሯ ከከበቧት እስከ ቤተ መቅደሷ ያለው መዋቅርና ከመንበሩ የሚፈልቀው*** "channel of spritual energy ***እንደ ቤት ወደድ አሊ ሚራ በሙሉ ልብ እንድንመሰክርለት ያደርገናል።***

***ይህም ብቻ አይደለም። የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ አቶ ታምራት ላይኔ በድሬደዋ ተገኝቶ ያካባቢውን ኦሮሞኛ ተናጋሪ በወገኑ ባማራው ክርስቲያን ላይ እንዲዘምት "አማራውን በሉት" ብሎ ባነሳሳበት ወቅት የአፋር ህዝብ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ አማራውን እንደታደገው የድሬደዋ ህዝብ እየመሰከረው ነው። ይህም የቤት ወደድ ሱልጣን አሊ ሚራ የሞራልና የዜግነት ፍቅር ውርስና ቅርስ ነውና ትዝታው በዚህ ቀውጢ ሰአት በሚነገረውና በሚጻፈው ሁሉ ላይ ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባውም።***

ይህች ዓለም በፀሐይ ዙሪያ እንደ እንዝርት ተሽከርክራ ዓመቱን ስትሻገር ቤተ ክርስቲያናችን ሰብስባ የያዘቻቸውን እነዚህን የመሳሰሉትን ትዝታወች ተሸክማ ነው። ክርስቶስ የተናገራቸው፣ ሀዋርያት ጻድቃን ሰማእታት መላእክት ያከናወኗቸው፣ ሊቃውንት አባቶቻችን የተናገሯቸው፣ ጀግኖች የሰሯቸው በእለታት በሳምንታትና በወራት ተደራጅተው በአውደ ምህረቱ ላይ የሚታወሱባቸ ድርብርብ በአላት(ዝክረ ነገራት) ሁሉ፣ ክርስቶስ እስኪመለስ በጸሀይ ዙሪያ ይሽከረከራሉ። ከነዚህ እለታት ውስጥ አንዷ በዓለም መጨረሻ ስለሚከሰቱት ምልክቶች በክርስቶስ፣ በሐዋርያት፣መካከል የተካሄደውን ጥያቄና መልስ የተሸከመችው **ደብረ ዘይት** በመባል የምትጠራው ያለፈችው እሁድ ነበረች።

በዚህች ቀን የሚነበበው ወንጌል እናትና አባቶቻችን ባንገታቸው አጥልቀው በደረታቸው ተሸክመው በየደረሱበት ለሚያነቧት መጽሐፍ ምንጭ የሆነው የመቴዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፬ ነው። ይህ ንባብ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ባሉት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ፊት ባለፈው እሁድ ተነበበ። ቁም ነገሩ ልማድ በመከተል ብቻ በልማድ መነበቡ አይደለም።

በአውደ ምህረት ላይ ቆሞ ለህዝብ ያነበበው ካህን መጀመሪያ ራሱን ከጨለማ ለማውጣት በተፈጥሮው ብርሃን ማፍቅ በማይችለው ዓይኑ ላይ "አንባቢ ያስተውል!" ሲል ክርስቶስ በፍካሬው የተናገረውን እንደመነጽር ባአይነ ልቡናው ላይ መሰካት አለበት። "አንባቢ ያስተውል!" የሚለውን የክርስቶስን ማስጠንቀቂያ በዓይነ ልቡናው ያልሰካ ካህን እንጀራ ፈላጊ ሰብሮ ገብ አነብናቢ እንጅ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ እውነተኛ ካህን አይደለም። አንባቢው ካህን መጀመሪያ "አንባቢ ያስተውል!" የሚለውን የኢየሱስን መፈክር በዓይነ ሕሊናው ላያ ከሰካ "በተቀደሰው ስፍራ ላይ በቆመው የጥፋት ርኩሰት" ቁጥጥር ስር መሆኑንና አለመሆኑን የማየት አቅም ይኖረዋል። ለምእመናንም በተቀደሰው ስፍራ ላይ የቆመውን የጥፋት ርኩሰት ማሳየት ይችላል።

# ፩ኛ. "በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ የሚታየው የጥፋት ርኩሰት(ማቴ ፳፬፡፲፭)" ባህርይ

James Redfield የተባሉ ሊቅ የተናገሩትን ጠቅሸ የኛ "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናት ብያለሁ። "ትዝታን አዝሎ በላያችን ደመና መስሎ የሚንሳፈፈው "የመንፈሳዊ ኃይል መጉረፊያ ቧንቧ" ጥንት የነበረውን ስሜት ቀስቅሶ ካዲሱ ክስተት ጋራ ያገናኝናል" እንዳሉት፣ ድንገተኛ አጋጣሚወች ሲገጥሙኝ ፊደል ከቆጠርኩበት ደብር ካስቆጠሩኝ መምህራን ጀምሮ እስከ ቤት ወደድ ሱልጣን አሊ ሚራ ንግግር ድረስ በሕይወቴ እየተደራረቡ ሲከመሩብኝ የኖሩት ሁሉ እርስ በርስ እየተጓተቱ ያንዣብቡብኛል።

በውስጤ ከተሸከምኩት ጋራ የሚጋጭና የማይጠቅም ነገር ስሰማና ሳይ በተለይ አባ ማትያስ ከንሳስ ላይ መጥተው በተቀደሰችው አውደ ምህረት ላይ ቆመው የሰሩትን ርኩስ ሥራና "በመጻሕፍት ላይ መጻሕፍት። በሊቃውንት ላይ ሊቃውንት ተተክተዋል" ብለው የተናገሩትን አጸያፊ ነገር ሳስበው ከሊቃውንት አበው ስሰማይ ከነበረው ትዝታ ጋራ የሚፈጥረው ግጭት እንደ ሰደድ እሳት ቦግ ይልብኛል።

በዚህ አጋጥሚ አባ ማትያስ የተሳሳተ ነገር ተሸክመው የቆሙባትን የተቀደሰች ስፍራ ለመግለጽ እገደዳለሁ። ይህች ስፍራ የከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የመሰረቷት የብዙ ሰዎችን ትዝታ የተሸከመች፣ ከተመሰረተች አመታት በኋላ የተመሰረተችበትን ዓላማና አቅጣጫ በመቀየር ያባ ማትያስን የተሳሳተ ትምህርት ተሸክማ በመንገድገድ ላይ ያለችው የከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያና

ናት። ይህች ስፍራ የተከበሩ አባት ቤት ወደድ አሊ ሚራ በፈታኝ ወቅት ግመሎቻችን በእጣኗ ያውቋታል ብለው ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን የተናገሩትን የምናስታውስባት ናት። ካባ ማትያስ ጋራ በጥፋት ታሪካዊ ትዝታ ያስተሳሰረችን የከንሳስ የከንሳስ ኪዳነ ምህረት ህንጻ። ከተከበሩ ቤት ወደድ አሊ ታሪክ ጋራ የተሳሰርንበትን የተቀደሰ ታሪካዊ ትዝታ ሳልጠቅስ ባልፍ አስተዋይ አንባቢ ይታዘበኛልና አላልፈውም።

የቤተ ክርስቲያኒቱን ሁለንተና የተገነዘቡ በከንሳስ ከተማ የሚኖሩ የተዋህዶ ልጆች ይህችን ሕንጻ ወደ ኦርቶዶክስነት ለውጠው ለመጠቅም ኃይላቸውን ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን በሰውበት ወቅት በከንሳስ ከተማ ነዋሪ የነበሩት <u>የተከበሩ የቤትወደድ አሊ ሚራ የእስልምና ሃይማኖት ልጆቻቸው የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖች በከንሳስ ይኖሩ ነበር። እነሱም ሃይማኖት ዜጎችን የማይከፋፍል መሆኑን የተገነዘቡ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሁሉ ዜጋ አቅማቸው በፈቀደላቸው ሲረዱ የነበሩ አቶ አብዲና ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ አናብ ናቸው</u>። በተለመደው ንጹሕ ህሊናና ብሄራዊ ፍቅራቸው የከንሳስ ኪዳነ ምህረትን ስንጀምር ያደረጉት አስተዋጽኦ ታሪክ የማይረሳውን የተከበሩ ቤት ወደድ አሊ ሚራ የተናገሩትንና የአፋር ህዝብ ለድሬ ደዋ ህዝብ ያደረገውን መታደግ ያገናኘ ታሪካዊ ሰንሰለት ነው።

አባ ማትያስ ከንሳስ መጥተው የመሳሰሉትን ብዙ ትዝታ በተሸከመችው በተቀደሰችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ መቅደስ የፈጸሙት፣ ከመሰረታዊው ተዋህዶ እምነትና ትምህርት የሚጋጭ መላው ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሊሰሙት የማይፈልጉት የማይውጥላቸው ርኩስ ነገር ነው። ይህን ርኩስ ከፋፋይ መርዝ በረጩበት ጊዜ Redfield "This can occur during any of the mentioned pathways to mystical" እንዳሉት የተማርኩት ነገረ መለኮት ካስተማሩኝ ሊቃውንት አበውና ከተማርኩባቸው መካናት ጋራ እንደ ደመና በላየ ላይ አንዣበው ከበቡኝ።

በተቀደሰችው ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ (<u>channel of spritual energy</u>) ላይ አቡነ ማትያስ ከሮማ ካቶሊክ እምነትና ትምህርት ከዚያም ይልቅ የራቀ የቡድሀ ሃይማኖት ይዘውብን መጥተው ቆሙ። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች "በዚህ በተቀደሰ ስፍራ ላይ እንዲቆም የሚፈቀደው የኦርቶዶክስን ተዋህዶ እምነት ለይተው አውቀው መመሰክር ለሚችሉ ሊቃውንት አበው እንጅ <u>እኛ እስካለን ድረስ እንደርሰዎ ያለ ሰው እንዲቆምበት አንፈቅድም ! ቦታዎም አይደለም!"</u> በማለት፣ ሸኘናቸው።

<u>የጥፋት ርኩሰት</u> ተሸክመው በተቀደሰችው ስፍራ በቆሙበት ጊዜ ያባረርናቸው አባ ማትያስ፣ ዛሬ ከብዙ ዓመታት በኋላ በመንበረ ፓትርክ ላይ ይህንኑ <u>የጥፋት ርኩሰት</u> ተሸክመው "በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፷፬ ድምጹ መረጠኝ" ብለው የተናገሩትን በአሜሪካ ሬድዮ ድምጽ ስሰማ "የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢ ያስተውል"(ማቴ ፳፬፥፲፭) የሚለው የኢየሱስ ፍካሬ ትዝ አለኝ።

ጌታችን ኢየሱስ በፍካሬው "የጥፋት ርኩሰት" ብሎ የገለጸው ሐሰት መናገርን ነው። "የሐሰት ምንጭ እውነት ለባህርዩ የማይስማማው በእውነት አይጸናም" (ዮሐ ፰፥፵፬) ብሎ ክርስቶስ በፍካሬው የመሰከረበት ዲያብሎስ ነው። ለዲያብሎስ መግለጫ ቅጽል የሚሆነው ርኩስ ነው። ከሱ የሚወጣው ሁሉ ሐሰት ስለሆነ ርኩስ ነው። በተቀደሰው ስፍራ <u>ቆሞው እየታዩ የጥፋት ርኩሰት የሚነገሩ</u> ሁሉ የዲያብሎስ '<u>ደቀ መዛብርት</u>' ናቸው ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ከሀሰተኛ መምህር ሐሰት የተማሩትን ለመግለጽ <u>"ደቀ መዛሙርት"</u> እየተባለ ሲነገር እሰማለሁ። <u>"ደቀ መዛሙርት"</u> ለጽድቅና ለእውነት ትምህርት ተሰልፈው ከክርስቶስ ለተማሩት ለሐዋርያት የተሰጠ ተስማሚ መግለጫ ነው። ይህን ለሚቃረን ከሀሰተኛ መምህር ሀሰትን ለሚማር ተማሪ ሊቀጸል አይገባም። የደቀ መዛሙርት ተቃራኒ (አፍራሽ) '<u>ደቀመዛብርት</u>' ነውና ተቃራኒውን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ '<u>ደቀመዛብርት</u>' የምትለው ቃል በዚህች ጦማር ተነገረች።

**'ደቀ መዛብርት'** የምትለው ሐረግ የምታመለክተው በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ የሚዋሸውንና እሱን አምኖ የሚከተለውን ሰው ነው። ይህ ግለሰብ የሹመት፥ የገንዘብና የሥጋዊ ጥቅማ ጥቅም ምንጭ ስለሆነ በግልና በድርጅት ሆነው ከሱ የሚገኘውን ጥቅማ ጥቅም የሚፈልጉ ሁሉ ጥራዝ ነጠቆች በራሳቸው እስኪዞ ርባቸው ድረስ፤ ጋሻውና ጃግሬው በመሆን ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደታየው ይህች ጦማር የተሸከመችውን እውነት በሚሸከሙት የሐሰት አውሎ ነፋስ በሚያበኑት ትቢያ ሸፋፍነው ለማስተባበል እንደሚነሱ የታወቀ ነው። ይህም ርኩስ ነገር ነው። በምንናገረውና በምንጽፈው ነገር ሁሉ ጥራዝ ነጠቆች የሚነጥቁት ጥራዝ መስጠት ተገቢ አይደለምና ርኩስ የምትለውን ቃል ያለቦታዋ ጠምዝዘው እንዳይወስዷት በርኩስ እና በቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነት ልግለጸው።

## ርኩሳትና ቅዱሳት

እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ ቅዱስ ነውና እኛ ርኩሳን የምንላቸው አሳማ፥ አይጥ፥ ፈረስ፥ በቅሎ፥ አህያና ጅቦች የመሳሰሉት ሁሉ ቅዱሳን ናቸው። በተፈጥሮው ርኩስ የሆነ ፍጥረት የለም። መጽሐፍ ርኩሳን ናቸው የሚላቸው ወደ ማይስማማቸው ቦታ ጎትተን ስናውላቸው ብቻ ነው። ያም ቢሆን **"ተውህበ ለነ ጸጋ ሕየንተ ጸጋ" (ዮሐ ፩፥፲፮)** የሚለውን "በኦሪት ላይ ወንጌል ተሰጠን" ብለን በምንተረጉም ክርስቲያኖች ብቻ የተወሰነ እንጅ፤ ርኩስነታቸው በዓለም ላለው ክርስቲያኑን ሁሉ አይደለም። ስለዚህ በባህላችን አንጻር የአገልግሎታቸውን ልዩነት ለመግለጽ ርኩሳን ብንላቸውም በተፈጥሯቸው ቅዱሳን ናቸው።

ኮት ሸሚዝ የምንለብሰው ርቃናችን ነውራችን ለመጋረድ ነው። ይሁን እንጅ ሰውነታችንን ለመጋረድ ሱሪና ኮት የምንለብስባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው። ሱሪ በምንለብስበት መንገድ ሸሚዝ ኮት መልበስ አንችልም። ይቀደዳል። ተቀደደ ማለት ረከሰ ማለት ነው። ሁሉም በተሰራለት ከገባና ከዋለ አገለገለ ማለትም ቅዱስ ነው። ቅዱስ የሆነ ሁሉ ያለመስመሩና ያለ ቦታው ከገባ ረከሰ ማለት ነው።

የነዚህን እንስሳት ሥጋ የሚበሉትን ክርስቲያኖች የምግባቸው ይዘት በኦሪቱ ባህል እንደኛ ምግብ ባለመቀረጹ ርኩሳን ናቸው ማለት ጸያፍ (ራስን ማርከስ) ነው። ጥሬ ሥጋ መብላት በኦሪት የተከለከለ ነው። ኦሪቱ የሚከለክለውን የአሳማና የፈረስ ሥጋ የሚበሉ ክርስቲያኖች፤ ኦሪት የሚከለክለውን ጥሬ ሥጋ እኛ ስንበላ አይተው ርኩሳን ናችሁ ሊሉን አይችሉም።ካሉን እነሱም ራሳቸውን አረከሱ። የየራሱን ባህል በመጠበቅ ተከባብሮ ከመኖር ይልቅ በባህል እርስ በርስ መነቃቀፍ፤ እርስ በርስ መራከስ ነው።

## በተልእኮ አንጻር ርኩስነትና ቅዱሳነት *ያለቦታው ተገጣውሮ የገባ አጉራ ነው።*

ወደ ሃይማኖታዊ ተልእኮ ስንመጣ የግብጽ እና የህንድ ወይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሰርስሮ ገብቶ ፓፓችሁ ነኝ ማለት እሱም ይረክሳል ቫቲካንንም ያረክሳል። እንደዚሁ ሁሉ የሮማ ካቶሊክን እምነት ለማራመድ ወደ ተዋህዶው ሰርስሮ ከገባ ራሱንም ቦታውንም አረከሰ። የርኩስ ትርጓሜ በዚህ መልክ ያለቦታው ተገጣውሮ የገባውን የሚገልጽ ነው።

የአቡነ ማትያስን ወደ ፓትርያርክነት መግባት በተዋህዶው አተረጌጎም ስንመለከተው፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መካከል የተገጣወረ ያለቦታው የገባ አጉራ ነው። ይህን አጉራ ጠርቦ አለዝቦና አለስልሶ ከመንበረ ፓትርያርኩ ጋራ ማንም ሊያቀራርበው፤ ሊያስታርቀውና ሊያስማማው የማይችል፡ ደጋግፈውና ሸፋፍነው ያስቀመጡት የአቶ አባይ ፀሐዬና የአቶ ስብሀት ነጋ ርኩስ ተግባር ውጤት ነው።

ርኩስ የሚባለው ወደ መንበረ ፓትርያርካችን ገብተው የቆሙብትን ሸፍጥ እንጅ በቦታው ላይ የተቀመጡትን አባ ማትያስንና ደጋግፎ ያስቀመጧቸውን የእነ አቶ ስብሀት ነጋንና የአቶ አባይ ፀሐዬን ሰውነት አይደለም። ህሊናቸውንና ተግባራቸውን እራሳቸው ቢያረክሱትም እግዚአብሔር የፈጠራቸው

ፈረሶችና አይጦችም በተፈጥሯቸው ርኩሳት ናቸው እንደማንላቸው ሁሉ እነዚህም ሰዎች በሰውነታቸው ርኩሳን አይባሉም። ከተፈጥሯቸው ጋራ እራሳቸው ይጋጩ እንጅ፤ እኛ በምንሰራውና በምንናገረው ሁሉ መጠንቀቅ አለብን።

አባ ማትያስ ቆመው የታዩበት ስፍራ በመላ ኢትዮጵያ ምድር ያለችው ደብር ዙሪያ የሚበቅሉትን እጸዋት ከሚለባለቡት ሳማ ቅጠሎች ጀምሮ በእሾሀቸው የሚዋጉ፤ በፍሬያቸው እየመገቡ በጥላቸው እየታደጉ ያሉትን ዋንዛ ዋርካና ሾላ ዛፎች፤ በአይን ከማይታዩ ተሐዋስያን ፍጥረታት ጀምሮ ያመረተችውን ማር ለመከላከል የምትናደፈውን ንብ፤ ማር ሳይሰሩ የሚናደፉትን ተርቦች ሁሉ ፍጥረታትን የወከለች ናት። ወደ ሰውነት ስንመጣ ሙታንና ህይዋናን ሰብስባ የምታስታውሰን "<u>channel of piritual Energy</u>"ናት።

ቤተ ክርስቲያናችን ከነዚህ አንዱ መነቀል መበጠስ መቆረጥ እንደሌለበት በቃለ ውግዘት ስታስተምር ኖራለች። በእጸዋትና በተሀዋስያን የሚደርሰውን ጉዳት የምታወግዝ ቤተ ክርስቲያናችን፤ እግዚአብሔር በአርያው በፈጠረው ሰው ላይ ሲከሰት፤ ድንጋይም ያምልክ ተራራም ያምልክ ለሰውነቱ በመከራው እንድንቆምለት የቤተ ክርስቲያናችን <u>ዶክትሪን</u> የሚያስገድደን ነው። ይህም ማለት <u>በጊዜ በቦታና በክስተት መሻሻል ከሚችሉት በቀኖና ከተካተቱት ትእዛዞች በላይ ነው ማለት ነው።</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የተጠመቁ ምእመናን ለዚህ ውግዘት ተገዥዎች በመሆን ተጎራብቷቸው ለሚኖረው ሌላ እምነት ለሚከተለው ሁሉ ደህንነት ዘበኞች ቢሆኑም አስፈጻሚዎች ሁላችንም የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናት ነን። <u>የመጨረሻውን ኃላፊነት ከነ ሙሉ ምሳሌነቱ የሚሸከመው ግን በተቀደሰው ስፍራ በመንበረ ፓትርያርኩ ላይ እንደ አባ ማትያስ ቅዱስ ነኝ ብሎ የቆመ ግለ ሰብ ነው።</u>

ይህ "በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ" የሚተየው አባት በሰው ላይ ይቅርና ቤተ ክርስቲያናችን አቅፋ በያዘቻቸው ፍጥረታት አይነት ላይ ርኩስ በሆነ በተሳሳተ ውሳኔ ማንም ጉዳት እንዳይፈጸምባቸው ጠበቃ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን እሾሁ እንዳይቆረጥ ሳማው እንደይነቀል ተናዳፊ ተሀዋስያን እንዳይታወኩ ብላ በውግዘት ያከበረችበት ምሳሌነቱ ላጠመቀቻቸው ልጆቿ ብቻ ሳይወሰን፤ እግዚአብሄር ለፈጠረው ዜጋ ሁሉ ተከላካይ ለመሆን ትምህርት ለመስጠት ነው። ለህንጻው አጥርና መከታ እንዲሆኑ ወይም ለጌጥ አይደለም። ፍካሬ ኢየሱስ <u>በተነበበችበት በዚህ አመት የደብረ ዘይት እለት ይህን ውግዘት ለማስከበር በተቀደሰው ስፍራ የቆሙትን አባ ማትያስን በፍካሬ ኢየሱስ እንመልከት</u>።

# <u>፫ኛ. አባ ማትያስ በፍካሬ ኢየሱስ</u>

በዚህ አመት በተቀደሰው ስፍራ ላይ ፍካሬ ኢየሱስ ሲነበብ ቆመው የታዩት አባ ማትያስ ናቸው። <u>የአባ ማትያስ በተቀደሰ ስፍራ በመንበረ ፓትርያርካችን ላይ መቆም በቤተ ክርስቲያናችን መርሆ ሲመዘን በኢትዮጵያዊ የምግብ ስሜትና በአህያ ሥጋ መካከል ያለው ልዩነት ነው።</u> "በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፷፮ ድምጹ መረጠኝ" ብለው በቦታው ላይ ቆመው ራሳቸው በራሳቸው ቢያውጁትም፤ <u>መጻሕቶቻችንን አቃጥለው ካላጠፏቸው፤ የተማረነውን የሚያስረሳ አልዛይመር የሚባለው በሽታ እኛንም ካላጠቃን በቀር ቅዱስ ልንላቸው አንችልም።</u>

አባ ማትያስ ሙያቸው ችሎታቸው ሞራላቸውና እምነታቸው ለቆሙበት ቅዱስ ስፍራ ተቃራኒ በመሆኑ ፍካሬ ኢየሱስ በማይስማማቸው በቀደሰው ስፍራ የቆሙ የጥፋት ሰው ናቸው ይላል። ፓትርክነታቸው የኢትዮጵያ ህዝበ ክርስቲያን የማይውጠው ከአሳማ ሥጋ የባሰ ነው። ፐትርክናቸውን የገለጽኩበትን ምሳሌ የአሳማው ሥጋ ሲብራራ፤ አባ ማትያስን በስሜ ይመጣሉ ብሎ ኢየሱስ በፍካሬው የገለጻቸው ሰዎች አንዱን ያደርጋቸዋል።

# “በስሜ ይመጣሉ”

የአባ ማትያስን ፓትርያርክነት ፍካሬ ኢየሱሱ እንዴት እንደሚገልጸው ስንመለከት፤ በውጩና በውስጥ ባለው ህዝብ መካከል የተፈጠረውን መለያየት የተጣሉትን ለማስታረቅ የሚጥሩትን ካህናት “መሰቀል ይገባቸዋል” በሚለው በአቶ ስብሀት ነጋ በተዘረጋ የጥፋት መረብ አባ ማትያስ ታዝለው መግባታቸውን እናያለን። የገቡበትን ሽፍጥ ያወቁ፤ በተቀደሰው ስፍራ ቆመው “በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፸፱ ድምጹ መረጠኝ”ብለው መዋሸታቸው ፍካሬ ኢየሱስ ፐትርክናቸውን የማይዋጥ ያሳማ ሥጋ አድርጎታል። በጥፋት ሰዎች እቅድ ተገፍተውና ተደፋፍረው እንደገቡ እያወቁ፤ ፐትርክናውን ሳይፈልጉት፡ ሳያስቡትና ሳይመኙት የወደቀባቸውን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ለመምሰል “በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፸፱ ድምጹ መረጠኝ” ማለታቸው ኢየሱስ “በስሜ ይመጣሉ” ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል።

አባ ማትያስ ካገር ውጭ ለሰላሳ ዘመን የኖሩ የአሜሪካ ዜጋ እንደሆኑ ሁሉ፤ ሰላሙን ለማስፈጸም ይንቀሳቀስ ለነበረው ቡድን ሊቀ መንበር የነበሩት ሊቀ ካህናት ኃይለ ስላሴም የአሜሪካ ዜጋ ናቸው። እኚህ ካህን የእርቁን ጉዳይ ይዘው አዲስ አበባ በሄዱ ጊዜ ዜግነትህን ስለቀየርክ ለዚህ ብቁ አይደለህም በመባል እንደተባረሩ የተነገረውን ያልሰማ የለም። አባ ማትያስም ሰምተዋል። <u>ያሜሪካ ዜግነት ለሽምግልና የማያበቃ ከሆነና ካገር የሚያስወጣ ከሆነ፤ የአባ ማትያስ አሜሪካዊነት ለፓትርያርክነት እንዴት ተስማሚ ሊሆን ቻለ?</u> ይህ ጥያቄ በያንዳንዳችን አዕምሮ ላይ ካለ፤ የነ ስብሀት ነጋ ሽፍጥ ካልጋረደው በቀር የአቡነ ጳውሎስን ከፋፋይነት የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ብቃት የሌሽነት ተረድተው ሲቃወሙ ከነበሩት ከአባ ማትያስ አዕምሮ ላይ ምን ሊደመስሰው ይችላል? ይህም ኢየሱስ “በስሜ ይመጣሉ” ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አድርጓቸዋል።

## <u>የአባ ሰላማ ድረ ገጽ ለአባ ማትያስ የሰጠው የሐሰት ምስክርነት</u>

አባ ሰላማ የሚባለው ድረ ገጽ ስለ አባ ማትያስ ለስፍራው ብቁነት በገለጸው ሽፍጡ (*በፓትርያርክ ምርጫ ላይ ማኀበረ ቅዱሳንን ለመቃወም ስልት አርጎ ባቀረበው*) http://www.abaselama.org/2013/02/blog-post_21.html#more) በ፲፬ አመታቸው የቅኔ ሊቅ እንደነበሩ ከዶ ክተር አየለ ሊቃውንቱን ሀዲሳቱን እንደተማሩና እንደገና ወደ ቅኔ ትምህርት ቤት እንደተመለሱ ይገልጽና፤ ሂብሩ አረበኛ እንደሚናገሩ የትምህርቱን አይነት ሳይገልጽ ማስትሬት እንዳላቸው መስክሮላቸዋል። እሳቸውም አላስተባበሉም። አባ ማትያስ ይህ ድረ ገጽ የመሰከረላቸው ሙያ ሊኖራቸው ይቅርና በልማድ የሚያነበንቡትን ቅዳሴ እንደማያውቁት እራሳቸው ያውቁታል። መላው የቤት ክርስቲያኒቱ ሰዎች ያውቁታል። በእውነት የኢትዮጵያ ህዝብ መርጧቸው ከሆነ፤ የአባ ሰላማ ድረ ገጽ በሰበከላቸው ሐሰት ተታሎ መርጧቸዋል ማለት ነው። ፍካሬ ኢየሱስ እንዳለው የጥፋት ርኩሳታቸውን ለማከናወን ወስነው የተነሱ በመሆናቸው የተሰበከላቸውን ሐሰት በዝምታ ተቀብለው በተቀደሰው ሥፍራ የቆሙ ስለሆነ የቅዱስነት ተቃራኒ ናቸው። <u>ይህም ኢየሱስ “በስሜ ይመጣሉ” ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል</u>።

ይህ ድረ ገጽ የነ ስብሀት ነጋ ማሚቶ ካልሆነ በቀር አባ ማትያስን ከዲስ ህዝብ፡ ከኔ እና ከከንሳስ ህዝብ የበለጠ አያውቃቸውም። ስለ አባ ማትያስ ያስነበበው ይህ የሐሰት ምስክርነት ድረ ገጹን የነ አቶ ስብሀት ነጋን ፍላጎት በህዝብ ላይ ለመጫን ታላቅ ተልእኮ ያለው አስመስሎታል። ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ድረ ገጽ ላይ የሚቀርበውን የሚያነብ ሁሉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ “<u>አንባቢ ያስተውል!”(፲፭ )</u> ብሎ በፍካሬው ያስጠነቀቀውን አይርሳ!

አባ ማትያስ አሜሪካ ሲኖሩ የቀሰሙት ያሜሪካ ሊቃውንት የሚጸየፉትን ነው። ልግለጸው። አሜሪካ “wonderful” የሚያሰኝ ገጽ እንዳለው ሁሉ “dark side” የሚባልም አለው። ማር የምትቀስመውን ንብ ለመሆን ለሚፈልግ፤ አሜሪካ ንብ ለማድረግ ኃይል አለው። ግም የምትቀስመውንም ዝምብ ለመሆን

ለሚፈልግም የሚሰጠው አያጣም። አሜሪካ ካፈራቻቸው አንህብት (ሊቃውንት) አንዱ Eric Schlosser የተባሉት "The dark side of the All American Meal" እያሉ የአሜሪካን ደካማ ጎኑን ገልጸውታል።

ደካማ ጎኑን በገለጹበት መጽሐፋቸው "This soda provide empty calories and have replaced far more nutritious beverage in the American diet. Excessive soda consumption in childhood can lead to calcium deficiencies and a great likelihood of bone fractures"( 54) ብለዋል። ይህም ማለት "የሚመረተው ሶዳ የሚባለው የመጠጥ አይነት የማይጠቅም ነገር ይሰጣል። እንዲያውም የሚጠቅመውን የመጠጥ ቦታ ተሻምቶ ወስዷል። በልጅነት ይህን አይነት ሶዳ በብዛት መጠጣት የካልስየም እጥረት ይፈጥራል። በመጨረሻም ያጥንት መሰነጣጠቅን ያስከትላል" ብለዋል።

አባ ማትያስ በአባ ሰላማ የተገለጸውን ሙያ ሊቀስሙ ይቅርና ሙያወች የሚፈልቁባቸውን ቦታዎች አልረገጡም። ስሜቱም የተፈጠረባቸው ሰው አይደሉም። ይልቁንም ባሜሪካ ቆይታቸው ሲጠጡ የኖሩት አጥንት ሰንጣቂ መርዘኛ ሶዳ ባሳደረባቸው ሱስ፣ መሰንጠቅ ሱስ የሆነበት መንግሥት በህዝብ እና በመሬት ላይ የሚፈጽመውን ስንጠቃ ለመርዳት በተቀደሰው ስፍራ የገቡ ናቸው። ይህም ኢየሱስ "በስሜ ይመጣሉ" ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል።

አባ ማትያስ በቤተ ክርስቲያናችን ሰላም እንደሌለ ያውቃሉ። ይህ የደፈረሰ ሰላም እንዲመለስ እና፣ ሳይመለስ የፓትርያርክ ምርጫ መፈጸም ቀርቶ መታሰብ የለበትም ብሏል። "ለሰላም እርቅ የጀመሩ ካህናት ይሰቀሉ" ሲል ከተናገረው ነፍሰ ገዳይ በቀር ይህን ያልደገፈ የለም። ይህን የህዝብ ፍላጎት ደምስሶ የገባና ያስገባውን "ወለእመ ተራድአ በመኳንንተ ዝንቱ ዓለም፡ወተሠይመ ለቤተ ክርስቲያን እምሃቤሆሙ ይትመተር ወይሰደድ ውእቱኒ ወኩሎሙ እለ ተሳተፍዎ"(ፍ.ነ. ፻፸፫) ብሎ የቤተ ክርስቲያናችንን መመሪያ ያወግዘዋል።

ይህንን በተመለከተ "ቄንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ" በሚል ርእስ የካቲት ፳፻፭ ዓ.ም. ተጽፎ በተለያዩ ድረ ገጾች በዓለም የተበተኑት የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ቀርቦ ተነቧል። አሁንም በመነበብ ላይ ነው። እሳቸው በነ ስብሀት ነጋ ብቻ ድጋፍ የቤተ ክርስቲያናችንን መርሆ ሰብረው የካህናቱን ማስጠንቀቂያ ጥሰው፣ የምእመናኑን ፈቃድ አፍርሰው በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆመዋል። ይህም ኢየሱስ "በስሜ ይመጣሉ" ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል።

"ጸልዩ በእንተ ሰላም" (ሥ. ቅ. ገጽ ፹፭፡ቁ ፶፰) ተብሎ ለሚታወጀው አዋጅ ምእመናን "ክርስቶስ አምላክነ ረሰየነ ድልዋነ፡ ከመ ንትአማኀ በበይናቲነ በአምኀ ቅድሳት" (ሥ. ቅ. ገጽ ፹፭ ቁ ፶፱) እያሉ ለእርስ ለርሳቸው ወድቀው በመነሳት ተሰጥአውን ከመመለሳቸው በፊት፣ "ከቂምና ከቅናት ሞትን ከምታለብስ ክፉ ነገር ከማሰብ ህሊናችንን አንጻልን" (ሥ. ቅ. ገጽ ፹፭ ቁ. ፶፯) እያለ ከፍ ባለ ድምጽ ካህኑ የሚያውጅበትን ስፍራ አባ ማትያስ ለመቆጣጠ ገብተዋል። ይህም አባ ማትያስን ኢየሱስ "በስሜ ይመጣሉ" ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል።

## በአማራው ላይ እየደረሰ ያለዉ "የመሬት መንቀጥቀጥ"

ይህች ጦማር ፍካሬ ኢየሱስ የያዘቻቸውን ምልክቶች ለማካተት በአቅሟ እንደምትገታ አስቀድሜ የተናገርኩትን ባለመዘንጋት፣ ኢየሱስ በፍካሬው "የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል"(ማቴዎስ ፳፬፡፯) የምትለዋን ላክልና ወደ መደምደሚየ እሸገራለሁ።

መሬት በጸነሰችው ቮልካኖ በተለያዩ ቦታወችና ወቅቶች መንቀጥቀጧ የተፈጥሮ ህግ ነው። አያስገርምም። የሚያስገርመው በአማራው ላይ ዛሬ የሚታየው ከተፈጥሮ ህግ ውጭ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ነው። በዚህ ሰሞን በአማራው ላይ የደረሰውን ሁኔታ ስሰማ ከጥቂት አመታት በፊት ከአባላቱ አንዱ ስለ ትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ጀግንነት ለመግለጽ ብሎ ተራራ አንቀጥቅጥ የሚል ቅጽል ሰጥቶ

የጻፈውን ማንበቤን አስታውሳለሁ። ይህ ሰው በሱ ቤት ድርጅቱ ስለፈጸመው ጀብዱ በውዳሴ ማቅረቡ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ግን እሱ የተመለከተበትን ድንቁርና ብሎ፣ ይልቁንም መሬትን ከመሬት፣ ህዝብን ከህዝብ ለመለያየት ጣሊያን ከተጠቀመበት ወራዳና ርካሽ ተግባር ከሚባለው ስንጠቃ ጋራ ያቆላልፈዋል።

## "ህዝብ በህዝብ . . . ላይ ይነሳል (ማቴዎስ ፳፬፡፯)"

ይህ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት በዘረጋው ተራራ አንቀጥቅጥ መርሀው ወገን በወገኑ ላይ ህዝብ በህዝብ ላይ እንዲነሳ እየቀሰቀሰ በሚያካሂደው መሬት አንቀጥቅጥ ርኩስ ተግባር በአማራው ላይ መሬት እንዲንቀጠቀትበት እያደረገ ነው። መሬት በጸነሰችው ቮልካኖ በተለያዩ ቦታወችና ወቅቶች መንቀጥቀጧ የተፈጥሮ ህግ ነው። አያስገርምም። እንዳልኩት፣ ፍካሬ ኢየሱስ "የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል" ያለው ዛሬ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት እንደሚያደርገው "ህዝብ በህዝብ ላይ ወገን በወገን" (፯) ላይ ተነሳስቶ የሚፈጽመውን ግፍና ቄካኔ አይነት እንጅ መሬት በጸነሰችው ቮልካኖ ስለሚከናወነው መንቀጥቀጥ አይደለም።

ፍካሬ ኢየሱስ የሚናገረው የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ህዝብ በቄካኔ ተነሳስቶ በህዝብ ላይ ሚፈጽመውን ግፍና መከራ የተንተራሰ ነው። በኢሳት አማካይነት እንደምንሰማው አማራው ወንድ የተወለደበትን አገሩን የሰራውን ቤቱን ያመረተውን መሬቱን እየተወ ወደ ማያውቀው ወደ አላደገበት አገር እንዲሰደድ እየተደረገ ነው። በሚፈጸምበት ግፍ መሬት ብቻ አይደለችም ጉልበቱ መላ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ነው። በዓለም ዙሪያ በስደት የሚኖረው ወገን ሁሉ በወገናዊ ስሜቱ በያለበት ሆኖ መንቀጥቀጡን እየተካፈለው ነው።

ህዝብ በህዝብ ላይ ተነስቶ ይህ አይነት መከራና ግፍ በሚፈጸምባቸው ቀናት "ለነፍሰ ጡሮች ለሚያጠቡ እናቶች ወዮላቸው"(ማቴ ፳፬፡፲፱) እንደለው፣ እርጉዟ፣ ወልዳ የተኛቸው አራሷ፣ አጥቢዋ እናት በአማራነቷ መሬት ተንቀጥቅጦባታል። የታቀፈችው ልጅ በበርሀ በስደት በክንዷ ላይ ሬሳ ሲሆን መሬት ብቻ አይደለም አንጀቷ መላ አካሏ ያጠባችበት ጠቷ፣ መንፈሷ ሁሉ ተንቀጥቅጦባትል። ይህን የሰሙ በዓለም ዙሪያ ተበትነው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እናቶችም ከሷ ጋራ ባላቸው ተፈጥሯዊ ግንኙነት የቆሙበት መሬት ተናውጾባቸዋል። መላ ሰውነታቸው ልጆቻቸውን እያጠቡ የሚያሰድጉበት ጡቶቻቸውም ተንቀጥቅጠውባቸዋል።

ይህ መንግሥት በመሬት አንቀጥቅጥ መርሀው የጥፋት ተልእኮ ለመፈጸም ህዝብን በህዝብ ላይ፣ ወገን በወግን ላይ እያነሳስ በህዝብና በህዝብ መካከል የማይታረቅ ቅራኔ እየፈጠረ ነው። በራሱ መንፈስ ያለውን ጥላቻ የዋሁን ህዝብ መርዞ፣ በየዋሁ ህዝብ ላይ አዘምቶ ከኑሯቸው እንዲያፈናቅሏቸውና እያሳደዱ እንዲገድሏቸው ያደርጋቸዋል። ይህ መሰርይ አድራጎቱን ሲታወቅበት ራሱ ያነሳሳውን ህዝብ ኮንኖ፣ ያዘመተበትን ህዝብ የሚደግፍ፣ ገላጋይና ታዳጊ መስሎ በመካከል ይገባል። በጉራፈርዳ እና በቤንሻንጉል-ጉምዝ አካባቢ በሚኖሩት አማሮች ላይ የሚካሄደው የዘር ማጥራት (Ethnic Cleansing ዘመቻ በቂ ማስረጃ ነው።

የቤንሻንጉል-ጉምዝ ህዝብ በዚህ መንግስት ግፊት ዛሬ ከሚያሳድደው ህዝብ ጋራ ለዘመናት ተሳስሮ ኖሯል። ዛሬ ይህ መንግስት በሰጠው ቅስቀሳ ተገፍቶ ባማራው ወገኑ ላይ ይህንንን አሰቃቂ ግፍ እንዲፈጽም አድርጎታል። ግፉ የደረሰበት የዋሁ ህዝብ በጥላቻና በምሬት የሚመለከተው በመርዘኞች ተገፋፍቶ ግፉን የፈጸመበትን የዋሁን የቤንሻንጉል-ጉምዝ ። የትግራይ ነጻ አውጭ መንግስት አማራውን ህዝብ በማያንሰራራበት ውድቀት ላይ እንዲወድቅ ካስደረገ በኋላ፣ተነሳስቶ ይህን ጥፋት ባማራው ላይ እንዲፈጽም የቀሰቀሰውን የቤንሻንጉል-ጉምዝ ህዝብ በዓለም መድረክ እየኮነነ ተፈናቃዮቹ አማሮች እንዲመለሱ እየጣርኩ ነው ይላል። ተፈናቃዮቹ እንዲመለሱ እየጣርኩ ነው እያለ በሌላ በኩል ደግሞ

ለየዋሁ አፈናቃይ ህዝብ መሬትህን ንብረትህን ሊወስዱብህ ተመልሰው ሊመጡብህ ነውና አትቀበል ይለዋል። በዚህ አወዛጋቢ ባህርዩ እሱ ሊወገዝበት ሊጠላበት ከህዝብ መካከልም ሊወገድበት የሚገባውን ወንጀል በየዋሁ ራስ ላይ እያሸከመው ነው። ጎጅና ተጎጅ ወገን መንግስት የሚያልፍ ወገን ግን ቀሪ ዘመድ መሆኑን ተረድቶ እርስስ በርስ ከመኮዳዳትና ቂምና ጥላችን ለልጅ ልጅ ከማትረፍ እንዲድን በዚህ ዘመን ያለ ሁሉ አስተዋይ ያላሰለሰ ጥረት ሊያደርግ ይገባዋል።

በአጸደ ካሉት ዛፎች በአንዱ ቅጠል ላይ ያለ አገባብ መበጠስ መቆረጥ እንዳይደርስ የተማርነውን ውግዘት አስፈጻሚዎች ሁላችንም የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናት ብንሆንም፤ የመጨረሻውን ኃላፊነት ከነ ሙሉ ምሳሌነት የሚሸከመው በተቀደሰው ስፍራ በመንበረ ፓትርያርኩ ላይ የቆመው "በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፳፪ ድምጹ መረጠኝ" ብለው የተናገሩት አባ ማትያስ እንደሆኑ "አንባቢ ያስተውል!"(ማቴ ፳፬፥፲፭ )

ዛሬ ራሷ ቤተ ክርስቲያናችን ባጠመቀቻቸው ልጆቿ ላይ ይህ ግፍ ሲደርስ በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆመው የሚታዩት አባ ማትያስ "ህዝብ በህዝብ ላይ ይነሳል"(፯) የሚለውን የክርስቶስን ፍካሬ ለመፈጸም በየጠረፉ በሚኖረው ህዝብ ላይ ሌላውን ጎሳ እየቀሰቀሰ የሚያዘምተውን መንግስት ለመደገፍ መሬት በተናወጸባት ሰውነቷ በሚንቀጠቀጠው አራስ ስም ከውስጥና ከውጭ በተሰበሰበሰበው ገንዘብ በተገነባው ፓላስ ውስጥ ከመሬት አንቀጥቃጮች ጋራ በመንፈላሰስ ላይ ናቸው። ይህም አባ ማትያስን ኢየሱስ "በስሜ ይመጣሉ" ብሎ በፍካሬው ከገለጻቸው ቢጽ ሀሳውያን አንዱ አርጓቸዋል። "ዘያነብብ ለይለቡ" ብሎ ኢየየሱስ በተናገረው ፍካሬ ይህችን ጦማር እደመድማለሁ።

# መደምደሚያ

## ፩. ምን መደረግ አለበት?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አንባቢ ያስተውል!" ሲል የተናገረው አንባቢ የሚያስተውለው ምንድነው? "በዚያን ጊዜ በይሁዳ የሚገኙ ወደ ተራራ ይሽሹ። በቤቱ ጣራ የሚገኝ ማንም ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣት አይውረድ። በእርሻ የሚገኝ ማንም ሰውል ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ (፲፮—፲፰)" ብሎ የተናገረውን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም መጨረሻ የሚታዩትን የመከራ አይነቶች ሲዘረዝር ቆይቶ "በዳንኤል የተነገረው የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ ስታዩ" ካለ በኋላ "አንባቢ ያስተውል!" ብሎ ኢየሱስ ያስጠነቀው ከላይ በተጠቀሰው ውስጥ የተካተቱት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት፦

ሀ. "ወደ ተራራ መሸሽ"።
ለ. "ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣ ከቤቱ ጣራ አይውረድ"።
ሐ. "ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ (፲፮-፲፰)" ያላቸው ናቸው።

መጀመሪያ "በዳንኤል የተነገረው" በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ የታየው የጥፋት ርኩስት ምን ነበረ? ሊቃውንት ቀደም ብለው ከተፈጸሙ ከሁለት ትንግርቶች ጋራ በማነጻጸር ያቆሙታል። እነዚህም ተፈጸሙ የሚባሉት፤ አንደኛው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ168 ዓመተ ምህረት ታሪክ ሲሆን፤ ሁለተኛ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ70 ዓመተ ምህረት የተፈጸመው ነው።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው ግን በዚሁ መጽሐፍ ላይ "ልክ በኖኅ ዘመን እንደሆነው ይሆናል"(፴፯) ብሎ ክርስቶስ የተናገራቸውንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ነገሮች በማየት፤ እነ ቅዱስ ጴጥሮስም "ፍርድ የሚጀመረ በእኛ ከሆነ ለእግዚአብሄር ወንጌል በማይታዘ ሰዎች ላይ የሚደርሰው መከራ እንዴትይልቅ የከፋ ይሆን?)"(፩ኛ ጴ ም፬፥፲፯-፲፱) ብለው ከተናገሩት ጋራም በማነጻጸር ክርስቶስ

ዳንኤልን ጠቅሶ ለንጽጽር እንዳቀረበው ጠቀሰው እንጅ በታሪክነት በዘመንና በቦታ የሚወሰን አይደለም" ይላሉ። ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ በየቦታው በሰው ላይ የሚፈጸሙት የመከራ አይነቶች ቀደም ብለው ከተፈጸሙት እጅግ የከፉ ይሆናሉ ብለው ይገልጹታል።

በፍካሬው የተገለጸው መከራ የሚፈጸመ በህዝብ ላይ ስለሆነ ህዝብ ሁሉ ማንበብና ማስተዋል ቢኖርበትም። ህዝብ ሁሉ አንባቢ ተናጋሪ አስተማሪ ሊሆን አይችልምና ለማንበብ ለመናገር ለማስተማር ለማንቃት በተቀደሰው ቦታ በቆሙት ካህናት ላይ የበለጠ ያተኩራል። ለምእመናንም <u>በተቀደሰው ስፍራ ላይ የቆመውን የጥፋት ርኩሰት</u> ማሳየት ያለበት ካህኑ ነውና "<u>አንባቢ ያስተውል!</u>" በሚለው በኢየሱስ መፈክር "**በተቀደሰው ስፍራ ላይ በቆመው የጥፋት ርኩሰት**" ቁጥጥር ስር መሆኑንና አለመሆኑን ከምእመናን በፊት አስቀድሞ ማየት ያለበት ካህኑ ነው።

**ሀ. "ወደ ተራራ መሸሽ"**። ሚሸሽበት ተራራ ከሀሰት ጨለማ ነጻ መውጫ ነው። "**ወጽድቅኒ ታግእዘክሙ**"(ዮሐ ፰፥፴፪) ብሎ ራሱ ኢየሱስ የተናገረው እውነት ነው። ደብራችን ተራራችን ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ እውነት (ነገረ መለኮት) ላይ የተመሰረተች ናት። ይህ ነገረ መለኮት አሐቲ ቅድስት" ከሚባሉት አቓዎቿ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ አንድ የሚደርጋት ነው። ይህ ሰንሰለት በአባ ማትያስ ይቅርና በማንም ሊቀየር ሊፈበጥስ የማይችል ዓለም አቀፋዊ ባህርይዋ (ተራራነቷ) ነው። <u>የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ሁሉ ከሚሰራጨው ሀሰትና ክፍፍል እየሸሸ ክርስቶስ እውነትና ጽድቅ እኔ ነኝ እያለ ስለራሱ ካስተማረው ሀዋርያት ከሰበኩት ጻድቃን ሰማእታት በደማቸው ከመሰከሩለት እነደነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የመሳሰሉ ሊቃውንት አበው የህይወት መስዋዕትነት ከከፈሉለት ተራራ ላይ ለመድረስ መታገል አለበት</u>።

**ለ. "ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣ ከቤቱ ጣራ አይውረድ"**። ጣራ አንዳይወርድ የተነገረው "ሰላም ሳይመሰረት የፓትርያርክ ምርጫ ሊደረግ ቀርቶ መታሰብ የለበትም" እያሉ እነ አቡነ አትናቴዎስ ያወጁት ነው። በፓትርያርክ ላይ የተመሰረተ ስድስት የሚል የቍጥር ቀኖና የለም" እያሉ በቤታችን መመሪያ መሰረት በቃለ ክህነታቸው የተናገሩት የእውነተኞች ካህናት ምስክርነት ነው። ይህን የተናገሩ ሁሉ ካህናት በጥቅም በሹመት ቃላቸውን አጥፈው የተናገሩትን ረስተው ማቄን ጨርቄን በማለት ካባ ማትያስ ጋራ ለመሰልፍ ከነበሩበት የሞራል ልዕልና (ጣራ) ራሳቸውን እንዳያወርዱ ማስጠንቀቂያ ነው።

**ሐ."ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ"** ከነ አቡነ አትናቴዎስ ከነ ሊቀ ካህናት መርዓዊ ተበጀ ጀምሮ ይህን ድምጽ ያሰማ ሁሉ በእምነት ያስተጋባው በሞራል ልዕልና ላይ ሰፈሮ ነው። ከነ አቡነ አትናቴዎስ ከነ ሊቀ ካህናት መርዓዊ ተበጀ ጀምሮ ይህን ቃል ያስተጋቡ ሁሉ ለጥቅምና ለማደር ብለው የተናገሩትን እውነት ሰርዘው ማቄን ጨርቄን በማለት ከነበሩበት የሞራል ጣራ ወደ ኋላ ማፈግፈግ የለባቸውም። "በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ህዝብ በ፷፪ ድምጹ መረጠኝ" እያሉ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ከገቡት ከአባ ማትያስ ጋራ ለመሰልፍ ከነበሩበት የሞራል ልዕልና ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ የተናገሩትን በመካድ ራሳቸውን ከትዝብት ላይ እንዳይጥሉ ኢየሱስ በፌካሪው "**ዘያነብብ ለይለቡ**" በማለት ያስጠነቅቃቸዋል።

"እንዲህ ያለ ፓትርያርክ አይተን አናውቅም" በምትለው ጦማር እስክንገናኝ ይቆየን።

**ይቆየን**

***ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድረ-ገጽ ይመልከቱ::***

http://www.medhanialemeotcks.org/